ETH-ADA

የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን
ETHIOPIAN ANTI-DOPING AUTHORITY

# የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን

## የህክምና ፈቃድ አሰጣጥ ምንድን ነዉ (ቲዩኢ) እና የአቀራረብ ደረጃዎች

አትሌቶች ህመም ሊሰማቸው ወይም ምን አይነት መድሃኒት መውሰድ የሚያስፈልጋቸው በሂደት ላይ የሚገኙ በሽታዎች ሊኖሩባቸው ይችላል፡፡ ሆኖም እነዚህ መድሃኒቶች በአለም አቀፉ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ (ዋዳ) የክልከላ ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ ከሆነ የህክምና ፈቃድ ለዛ አትሌት እነዚህን መድኃኒቶች እንዲጠቀም እና መወዳደር እንዲችል ወይም የፀረ አበረታች ቅመሞች ህግ (ADRV) ባልጣሰ መልኩ እንዲጠቀም ፈቃድ ሊሰጥም ይችላል፡፡ እነዚህ ለፈቃድ የቀረቡ መድሃኒቶች የህክምና ፈቃድ ኮሚቴዎች (TUEC) አባላት በሆኑ ሀኪሞች ምርመራ ይደረግባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የሚሰጠዉ ህክምና ፈቃድ ስልጣን በብሔራዊ ደረጃ በሚከናወኑ ውድድሮች ከውድድር በኋላ (ዉጪ) ባሉ ምርመራዎች ላይ ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡

## የህክምና (ቲዩኢ) ፈቃድ ለመስጠት የሚያገለግሉ መስፈርቶች

የቲዩኢን ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው (ለበለጠ ዝርዝር በዋዳ አለም አቀፍ ስታንዳርድ ለቴራፓቲክ አጠቃቀም ልዩ መብቶች) (አይኤስቲዩኢ) አንቀጽ 4.2ትን ይመልከቱ፡(WADA International Standard for Therapeutic Use Exemptions (ISTUE)

- አትሌቱ በግልፅ የተመለከተ የምርምራ ውጤት እና እነዚህን የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ለመውሰድ የሚያበቃ የህክምና መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡
- ይህ ቴራፓቲክ ንጥረ ነገር ያለበት መድሃኒት አገልግሎት ከአትሌቱ መደበኛ የጤና ሁኔታ ባሻገር በክህሎቱ ላይ ልዩ የሆነ ጉልበት ወይም ሀይል የሚሰጠው መሆን የለበትም፡፡
- ይህ የተከለከለው ንጥረ ነገር ለተመለከተው ህክምና አገልግሎት የሚውል ከሆነ ሌላ አማራጭ የተከለከለ ንጥረ ነገር ጥቅም ላይ መዋል የለበትም፡፡
- ይህ የተከለከለው ንጥረ ነገር አስፈላጊነት ከዚህ በፊት በቲዩኢ ከተሰጠው ፈቃድ በፊት ለነበረ ህክምና ወይም በህክምና ፈቃድ ተከልክሎ ለነበረ ህክምና አገልግሎት አይውልም፡፡

በእነዚህ አራት መስፈርቶች የህክምና ፈቃድ ለማግኘት በብሔራዊ ደረጃ የሚገኙ አትሌቶች ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ማመልከት ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው አትሌቶች የህክምና (ቲዩኢ) ፈቃዶችን ለአለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች እና/ወይም ለታላላቅ ክንዋኔ (ውድድር) አዘጋጆች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## የህክምና ፈቃድ እነ ማን ማመልከት ይኖርባቸዋል? የት እና መቼ ማመልከት አለብን?

በፀረ ዶፒንግ ህጎች የሚገዙ አትሌቶች የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም የህክምና ዘዴዎችን ለመጠቀም  እና ወደ ኋላ ለወሰዱት መድሀኒት የቲዩኢ ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህ አትሌቶች በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን መለየት አለባቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ አትሌቶቹ ሊጠቀሙት ያሰቡት መድሃኒት ወይም የህክምና  ዘዴ  በዋዳ የክልከላ ዝርዝር ውስጥ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

እነዚህ አትሌቶች ለሀኪሞቻቸው በፀረ-አበረታች ቅመሞች ድንጋጌዎች የሚገዙ አትሌቶች መሆናቸውን ማሳወቅ አለባቸው። እነርሱ እና ሀኪሞቻቸው በ https://www.wada-ama.org/en/prohibited-list ድረገፅ ውስጥ በመግባት የትኛው ንጥረ ነገር/የህክምና ዘዴ እንደታዘዘ ማረጋገጥ አለባቸው። መድሃኒቱ የያዘው ንጥረ ነገር ወይም የህክምና ዘዴ የተከለከለ ከሆነ ባልተከለከሉ አማራጮች ላይ ውይይት ማድረግ አለባቸው። ሆኖም ሌሎች ያልተከለከሉ ንጥረ ነገር አማራጮች ከሌሉ የህክምና ፈቃድ ያመልክቱ። ያስታውሱ አትሌቶች ቀዳሚ ሀላፊነት አለባቸው። አስቸጋሪ ሁኔታዎች ካጋጠማቸው የኢትዮጵያ  ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣንን ያናግሩ።

በዚያም ከኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ጋር ስለ ውድድሮቻቸው ደረጃ እና ስለ የህክምና ፈቃድ አፈፃፀም መስፈርቶች ግንኙነት ማድረግ አለባቸው።

የብሄራዊ ደረጃ አትሌት መሆናቸው ከተወሰነ እንደ አስፈላጊነቱ በልዩ ድንገተኛ ሁኔታ ወይም ልዩ አስተያየት በሚደረግባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር አስቀድመው ለኢትዮጵያ ፀረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ማመልከት ይኖርባቸዋል።

በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ህግ መሰረት ብሔራዊ ደረጃ አትሌት የሚባለው፡-

- በግሉ ወይም በቡድን ደረጃ ኢትዮጵያን በመወከል በአለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም አትሌት
- በእያንዳንዱ ብሔራዊ ስፖርት ቡድኖች ውስጥ የሚካተት ማንኛውም አትሌት
- በኢትዮጵያ መንግስት፣ በብሄራዊ ፌዴሬሽኖች፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና በሌሎች ድርጅቶች በሚዘጋጁ ብሄራዊ ውድድሮች እና ክንዋኔዎች ውስጥ ተሳታፊ የሆነ አትሌት

- ማንኛውም በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኖቻቸው አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው አትሌቶች ተብለው የተለዩ አለም አቀፍ አትሌት ተብለው የሚቀጠሩ ሲሆን (ብሔራዊ አትሌቶች አይደሉም) ለዚህ ፀረ-አረበታች ቅመሞች ድንጋጌዎች እንዲሁ ይወሰዳሉ፡፡
  በውድድሮች ውስጥ አገልግሎት ላይ ለሚውሉ ንጥረ ነገሮች ብቻ ከተከለከሉ ከቀጣዩ ውድድራቸው 30 ቀን አስቀድሞ የህክምና ፈቃድ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እባክዎ ከታች "ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ህክምና ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ እንዴት ማመልከት ይቻላል?" የሚለውን ይመልከቱ፡፡

ደረጃቸው ከላይ በተገለጸው መሰረት "ከብሔራዊ ደረጃ" አትሌት በታች ከሆኑ ለህክምና ፈቃድ በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ወይም በሌላ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ድርጅት ምርመራ ከተደረገባቸው በኂላ የማመልከት መብት አላቸው፡፡ እነዚህ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው አትሌቶች የሚባሉት በክልል ደረጃ ወይም ከዚያ በታች በሆኑ አካላት በሚዘጋጁ ውድድሮች ላይ የሚሳተፉ ናቸው፡፡

የክልል ደረጃ አትሌቶች በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የብሄራዊ ደረጃ አትሌቶች ማሟላት ያለባቸውን እና በአለም አቀፍ የህክምና ፈቃድ አሰጣጥ ስታንዳርድ አጠቃቀም ልዩ መብቶች (አይኤስቲዩኢ) እና በአለም አቀፍ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ኮሚቴ የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልተው ምርመራ የማድረግ መብት አላቸው፡፡ ሆኖም በክልል ደረጃ የሚገኙ አትሌቶች ከብሔራዊ ደረጃ በታች የሚወዳደሩ በአለም አቀፍ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ ኮሚቴ ድንጋጌ መሰረት ከቅድመ ህክምና ፈቃድ ዉጪ ለፈጣን የህክምና ፈቃድ ማመልከት ይችላሉ፡፡

## ጠቃሚ ማስታወሻ

በኢትዮጵያ ፀረ- አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የሚሰጠው የህክምና ፈቃድ ዋጋ የሚኖረው ለብሄራዊ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ አትሌቶች አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው አትሌቶች ከሆኑ ወይም በዋና ክንዋኔ ድርጅት በተዘጋጁ ውድድሮች ላይ የሚሳተፉ ከሆነ ይህ ምርመራ ውጤት በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች ወይም በዋና የክንዋኔ ድርጅት ያልታወቀ ከሆነ በስተቀር ዋጋ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ አትሌቶች በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተሰጠዉ የህክምና ፈቃድ በእነዚህ አለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች ወይም ዋናውን ክንዋኔ አዘጋጆች ተቀባይነት እንዳላቸው የማረጋገጥ ሀላፊነት አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የአትሌትነት ደረጃራቸውን እንዲሁም የቲዩኢ ማመልከቻ መስፈርቶቻቸው ላይ እገዛ የሚያደርግላቸው ከሆነ እነርሱም በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተሰጣቸውን የህክምና ፈቃድ ለአለም አቀፍ ደረጃዎች ወይም ለዋና ክንዋኔ አዘጋጅ ድርጅት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

እባክዎ
ሔለን ገ/ሚካኤል
ስልክ፡ +251911955649
ኢሜይል፡ tue@ethnado.org
ይሃ ሲቲ ሴንተር, 8ኛ ፎቅ ላይ በአካል በመቅረብ ያናግሩን

**ክልክላ ከመጣሉ በፊት ለሚደረግ የህክምና ፈቃድ ማመልከት**

አትሌቶች ክልከላ ከመጣሉ በፊት ለሚሰጥ ህክምና ፈቃድን በተመለከተ ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ማመልከት የሚችሉት

- ባጋጠማቸው ድንገተኛ ወይም አስቸኳይ የጤና ህክምና ሲያስፈልጋቸው
- በቂ ጊዜ ሳይኖራቸው፣ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻቸውን ለማቅረብ የሚከለክላቸው አጋጣሚ ወይም ልዩ ሁኔታዎች ሲደርሱባቸው ወይም ከምርመራው በፊት መገምገም ካለበት
- በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ፀረ አበረታች ቅመሞች ህግ መሰረት በቅድሚያ ለህክምና ፈቃድ ማመልከቻ የማይፈቀድላቸው ወይም የማይገባቸው ከሆነ
- የተመረመሩ እና በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች ወይም በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የስልጣን ወሰን ስር ያልሆነ ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው አትሌቶች ከሆኑ
- የአበረታች ቅመም ምርመራ ዉጤታቸዉ ፖዘቲቭ ከሆነ በውድድሮች ላይ ብቻ የተከለከሉ ቅመሞችን ከውድድር ጊዜ ውጪ ተጠቅመው ከሆነ (ለምሳሌ ግሉኮኮርቲኮይድስ)

**በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች እና ሌሎች የአለም አቀፍ ህክምና ፈቃድ አሰጣጥ ድንጋጌዎችን** ባልጣሰ መልኩ ለህክምና የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ወይም የህክምና ዘዴዎች በህጉ ላይ ካለ ይህንን ክልከላ ከመጣሉ በፊት(ሪትሮአክቲቭ) ለሚሰጥ ህክምና ፈቃድ አለመስጠት ፍትሀዊ አይሆንም፡፡

ይህ ልዩ ክልከላ ከመጣሉ በፊት(ሪትሮአክቲቭ) የሚሰጥ ህክምና ፈቃድ የሚሰጠው በዋዳ ቅድሚያ ፈቃድ (እና ዋዳ እንደራሱ መብት በኢትዮጵያ ፀረ- አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ውሳኔ የመፍቀድ ወይም ውድቅ የማድረግ መብት አለው)

**ጠቃሚ ማስታወሻ፡**

የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም የህክምና ዘዴዎችን ያለ ህክምና ፈቃድ መጠቀም አለም አቀፍ የፀረ-አበረታች ቅመሞች ድንጋጌ መጣስ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የወዲያው ህክምና ፈቃድ ከናሙና ስብሰባ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ አትሌቶች የህክምና ፋይል ማዘጋጀት እና ለግምገማ በሚፈለግበት ጊዜ ለማቅረብ ዝግጁ እንዲሆኑ በጥብቅ ይመከራል፡፡

**የህክምና ፈቃድን ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን እንዴት ማመልከት ይቻላል?**

የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የህክምና ፈቃድ ማመልከቻዎች ከተፈላጊ የህክምና ማስረጃዎች ጋር በፀረ-አበረታች ቅመሞች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስርአት (አዳምስ) በኩል እንዲቀርቡ ያበረታታል፡፡ ሆኖም የአዳምስ አካውንት ከሌልዎት እባክዎ ሔለን ገ/ሚካኤል ን በ+251911955649 ወይም በኢሜይል አድራሻ tamhel95@gmail.com አግኝተው የአዳምስ አካውንት ያስከፍቱ፡፡ ወይም የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ፣ ኤሌክትሮኒክስ ቅጂ ከhttps://ethnado.org.et/wp-content/uploads/2019/03/ETH-ADA-tue_application_form_-_electronic_version-2022.pdf ዳውንሎድ በማድረግ ካጠናቀቁ በኋላ ፈርመው ከአስፈላጊ የህክምና ማስረጃዎች ጋር በ tamhel95@gmail.comይላኩት፡፡ አለበለዚያ በአካል ይሄ ሲቲ ሴንተር 8ኛ ፎቅ ያቅርቡ፡፡

የህክምና ፈቃድ ማመልከቻዎ በህጋዊ ቅፅ በካፒታል ሌተር ወይም ታይፕ በማድረግ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የህክምና ማስረጃዎቹ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

- የተሟላ የህክምና ታሪክ የኦሪጅናል ምርመራ ሀኪም ሰነድ ጨምሮ (ከተቻለ)
- የሁሉም ምርመራ ውጤቶች፣ የላብራቶሪ ምርመራዎች ወይም ኢሜጂንግ ጥናቶች

**ከማመልከቻ ጉዳዩ ጋር የተገናኙ**

ከህክምና ፈቃድ ጋር በተገናኘ ማናቸውም ወጪዎች ከነተጨማሪ ተፈላጊ የህክምና ምርመራዎች፣ ፍተሻዎች፣ ኢሜጂንግ ጥናቶች ወ.ዘ.ተ ጨምሮ የመሸፈን ሀላፊነቱ የአትሌቶች ነው፡፡

ማንኛውም ያልተሟላ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ የማይስተናገድ ሲሆን በድጋሚ እንዲገባ ወይም ተሟልቶ እንዲመጣ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

ማንኛውም ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ያለ ህክምና መረጃዎች የቀረበ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ወደ አትሌቱ የሚመለስ ሲሆን ሂደቱ አይከናወንም፡፡

አትሌቶች ሀኪሞቻቸውን ሁሉንም የህክምና መረጃዎች እና የምርመራ ውጤቶች፣ የመድሃኒት ዝርዝሮች እንዲሁም በህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ቅፁ ላይ በተተወው ክፍት ቦታ ላይ የሀኪሞች ማረጋገጫ እንደተሟላ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

ሀኪምዎ ትክክለኛውን የህክምና ሰነዶች መስጠትን በተመለከተ ለማገዝ ከዋዳ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ቼክ ሊስት Checklists for TUE applications ለመመሪያዎች እና ድጋፎች እንዲመለከቱ እንዲያደርጉ እና ለተለመዱ ልዩ የህክምና ሁኔታዎች፣ ህክምናዎች፣ ንጥረ ነገሮች ወዘተ የቲፒጂን ውሳኔ ለማገዝ መቅረብ ያለባቸው የህክምና መረጃዎች Medical Information to Support the Decisions of TPGs የሚለውን ድንጋጌ ይመልከቱ።
የሚላክልዎትን የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ እና የህክምና መረጃዎች ቅጂ ይያዙ።

## በዋና ዋና ክንዋኔዎች(ውድድር አዘጋጆች) ላይ ምን ይፈጠራል?

የዋና ዋና ክንዋኔዎች ድርጅት አትሌቶች የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም የህክምና ዘዴዎችን ከክንዋኔው ጋር በተገናኘ የመጠቀም ፍላጎት ካላቸው ለህክምና ፈቃድ ተቀባይነት ማግኘት ማመልከት እንዳለባቸው ይደነግጋል።

አትሌቶች በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተሰጠ የህክምና ፈቃድ ካላቸው እንዲሁም አትሌቶቹ በዋና ዋና ክዋኔዎች ለምሳሌ የኦሎምፒክ ጨዋታዎች ላይ የሚሳተፉ ከሆነ ስለ ህክምና ፈቃድ አሰጣጥ ተቀባይነታቸውን አትሌቶች ከዋና ክዋኔዎች(ውድድር አዘጋጆች) ማግኘት ይጠበቅባቸዋል።

## ስለ ህክምና ፈቃድ ማመልከቻቸው አትሌቶች ውሳኔ የሚያገኙት መቼ ነው?

የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የህክምና ፈቃድ ውሳኔ በተቻለ ፍጥነት መድረስ ያለበት ሲሆን ብዙ ጊዜ የተለመደው የተሟላ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ከተፈላጊ የህክምና መረጃዎች ጋር በቀረበ በ21 ቀናት ውስጥ ነው።

## አትሌቶች የህክምና ፈቃዳቸውን ማደስ ከፈለጉስ?

እያንዳንዱ የህክምና ፈቃድ ልዩ የቆይታ ጊዜ ያለው ሲሆን ይህ ጊዜ ሲያበቃ ወዲያውኑ አገልግሎቱ ያበቃል። ሆኖም አትሌቶች የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወይም የህክምና ዘዴዎችን መጠቀማቸውን ለመቀጠል ከፈለጉ ከማብቂያው ቀን በፊት አዲስ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ከተሻሻለ የህክምና መረጃ ጋር ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ይህም አሁን በስራ ላይ ያለው የህክምና ፈቃድ ከማብቃቱ በፊት ተፈላጊውን ውሳኔ ለመስጠት በቂ ጊዜ እንዲገኝ ያስችላል።

__ጠቃሚ ማስታወሻ፡-__

ከናሙና ስብሰባ በኋላ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን መጠቀም፣ የመያዝ ወይም የማስተዳደር ሁኔታው አትሌቱ በሞላው የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ መሰረት መሆን አለበት፡፡ ሆኖም አትሌቶቹ ከተጠቀሰው ንጥረ ነገር የተለየ መጠን፣ ድግግሞሽ፣ መንገድ ወይም የማስተዳደር ቆይታ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ሌላ አዲስ የህክምና ፈቃድ መሙላት እንዳለባቸው በማወቅ የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣንን ማግኘት አለባቸው፡፡ አንዳንድ ንጥረ ነገሮች እና መጠኖች ለምሳሌ፡- እንደ ኢንሱሊን ያሉ በህክምና ሂደት ወቅት ራሳቸውን የሚቀይሩ በመሆኑ በአካሚው ሀኪም የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ስፍራ ላይ መገለፅ ያለበት ሲሆን ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ህክምና ፈቃድ ሰጪ ኮሚቴ ተቀባይነት ያገኛሉ፡፡

## __የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገስ?__

የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ውድቅ በሚደረግበት ጊዜ ይህ ውሳኔ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገበትን በቂ ማብራሪያ ይይዛል፡፡ ሆኖም ይህ ለአትሌቱ ግልፅ ካለሆነ አትሌቶች የህክምና ፈቃዱ ለምን እንደተከለከለ የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን በማግኘት ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

አልፎ አልፎ ግልጽ መረጃዎች፣ የምርመራ ውጤቶች፣ የላብራቶሪ ውጤት መጥፋት ወ.ዘ.ተ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን በድጋሚ ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡ አለበለዚያ አትሌቶች ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ ማለት ይችላሉ፡፡

## **የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተሰጠው የህክምና ፈቃድ በአለም አቀፍ ፌዴሬሽኖች ተቀባይነት ካላገኘስ?**

እንደዚህ አይነት ማመልከቻዎች ተቀባይነት አለማግኘታቸውን በመጥቀስ አትሌቱ ወይም የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ጉዳዩን በተመለከተ ለዋዳ የሚያመለክቱበት 21 ቀናት አላቸው፡፡ አትሌቱ ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን እንዳቀረበው አይነት የህክምና ፈቃድ አጠቃቀም ፈቃድ ኮሚቴ ያቀረበውን አይነት መረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ ኦንላይን ዘዴ ወይም በሚከተሉት የተመዘገበ ፖስታ አድራሻ መላክ ይኖርበታል፡-

ዋዳ የህክምና መምሪያ
የአለም አቀፍ  የፀረ- አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ
ስቶክ ኤክስቼንጅ ታወር
800 ፕሌስ ቪክቶሪያ (ቢ.ቁ 1700)
ፖ.ሣ.ቁ. 120
ሞንትሪያል (ኪዩቤክ) ኤች4ዜድ 1ቢ7
ካናዳ

ማመልከቻው በድጋሚ እንዲታይ ማመልከቻ የሚቀርብበት ኢሜይል አድራሻ medical@wada-ama.org የዋዳ ውሳኔ በሂደት ላይ ባለበት ጊዜ በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተሰጠው ፈቃድ ለብሄራዊ ደረጃ ከውድድር በኋላ በሚደረግ ምርመራ መሰረት ውድድሩ ላይ አትሌቱ እንዲሰለፍ  በቂ ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ለመልሶ እይታ ለዋዳ ካልተላከ የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን ኦሪጅናል የህክምና ፈቃድ ለብሄራዊ ደረጃ ውድድር እና ከውድድር ውጪ በኋላ በሚደረግ ምርመራ መሰረት አትሌቱ በውድድሩ ላይ መሳተፍ ይችላል ወይም አይችልም የሚለውን የመወሰን መብት አለው፡፡

## የአትሌቶች የህክምና መረጃዎች በሚስጥራዊ ዘዴ ይያዛሉ?

ሁሉም ከአትሌቱ ጋር የተያያዙ በየህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ላይ የሰፈሩ መረጃዎች ከአባሪ የህክምና መረጃዎች እንዲሁም ሌሎች የአትሌቱን የህክምና ፈቃድ ጥያቄ ግምገማ ጋር የተያያዙ ማናቸውም መረጃዎች በሙሉ በጥብቅ ሚስጥራዊነት የሚያዙ ሲሆን እንዲሁም በጸረ-አበረታች ቅመሞች ስራ አመራር እና አስተዳደር ስርአት (አዳምስ) የህክምና ፈቃድ እና በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ETH-ADA tue_application_form_-_electronic_version  2022 መሰረት ይስተናገዳል፡፡ ሁሉም የህክምና ፈቃድ ሰጪ ኮሚቴ አባላት ወይም  ሌሎች የአትሌቶችን የህክምና ፈቃድ ጥያቄ እና ተያያዥ መረጃዎችን (በአትሌቱ ማረጋገጫ ላይ እንደሰፈረው) የሚቀበሉ አካላት እነዚህን ሚስጥራዊ መረጃዎች የመያዝ ፕሮፌሽናል ወይም የውል ግዴታ አለባቸው፡፡

የአትሌቱን ማረጋገጫዎች በጥንቃቄ ይመልከቱ፡፡ በተለይ አትሌቶች ለኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የህክምና አጠቃቀም ልዩ መብት ኮሚቴ ያቀረቧቸውን መረጃዎች በአትሌቱ ማረጋገጫ መሰረት ውድቅ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት ያላቸው ሲሆን ሆኖም በዚህ ጊዜ የእርስዎ የህክምና ፈቃድ ማመልከቻ ፈቃድ ሳይሰጠው  ውድቅ የተደረገ እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡

በአለም አቀፍ የግል መረጃ  እና ግለኝነት ጥበቃ ስታንዳርድ መሰረት ማንኛውም የአትሌት ህክምና ፈቃድ ጥያቄ ጋር የተገናኙ መረጃዎች በኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን እንዲሁም በሌሎች ስልጣን ያላቸው አካላት ዘንድ ጉዳዩን ለማከናወን ተፈላጊ ከሆነበት ቀን በላይ ተይዘው አይቆዩም።

**የግንኙነት መረጃዎች**

ከኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የግል መረጃ አያያዝ ልማድ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ privacy@ethnado.org ያግኙ።

ስለ ህክምና ፈቃድ ማመልከት ስለሚገባው ድርጅት ጥርጣሬ ካልዎት ወይም ማንኛውም ከ ህክምና ፈቃድ ጋር  የተገናኙ ጥያቄዎችን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፀረ-አበረታች ቅመሞች ባለስልጣንን በሚከተሉት አድራሻዎች ያግኙ።

ሔለን ገ/ሚካኤል

ስልክ፡ +251911955649

ኢሜይል፡ tue@ethnado.org

ይሃ ሲቲ ሴንተር  8ኛ ፎቅ ላይ በአካል በመቅረብ ማግኘት ይችላሉ

## ሌሎች ጠቃሚ ሊንኮች፡

የዋዳ አለም አቀፍ የቴራፓቲክ አጠቃቀም ልዩ መብት ስታንዳደርድ (አይኤስቲዩኢ)

WADA International Standard for Therapeutic Use Exemptions (ISTUE)

ስለ ቲዩኢ ማመልከቻ የዋዳ ቼክሊስት

WADA Checklists for TUE Applications

የዋዳ የ 2013 ዓ.ም የዋዳ አለም አቀፍ የቴራፓቲክ አጠቃቀም ልዩ መብት ስታንዳደርድ (አይኤስቲዩኢ)

WADA Guidelines for the 2021 International Standard for Therapeutic Use Exemptions (ISTUE)

የዋዳ ፀረ- አበረታች ቅመሞች ትምህርት እና መማር (ኤዲኢኤል)

WADA Anti-Doping Education and Learning (ADEL)